# የኤደን ኪዳን

አንድን ጉዳይ የምናይበት፤ አይተንም ውሳኔ ልንሰጥበት የምንችልበት ወንፊት ወይንም ማጣሪያ ያስፈልገናል። በዘፈቀደ ተነስተን ፤ በስመነጋ የምናደርጋቸው ፤ የምንወስናቸው ውሳኔዎችና ድርጊቶች በሕይወታችን ላይ ትልቅ አደጋ ሊያመጡ የሚችሉ ስለሚሆን ከወሰንን በኋላ የሕይወት ጠባሳ ሆነው ይቀራሉ። ይህ እንዳይሆን ከወዲሁ ጥንቃቄ ልናደርግ ይገባናል።

ጋብቻን (ትዳርን) ጀምሮ ማቋረጥ፤ መተው፤ ፈትቶ ወይንም ተፋቶ መሄድ ለእኛ በተለይ ጋብቻችንን የሰጠን እግዚአብሔር ነው ለምንል አልተሰጠንም። የተባልነው ወይንም የተሰጠን ዳር እንድናደርስ፤ እስከሞት ድረስ አብረን ልንኖር፤ በእግዚአብሔርና በሰው ፊት የገባነውን ቃልኪዳን ልንፈጽም ነው። ይህ የጋብቻ ህይወት የትኛውም ምክንያት ሊያግደው ሊያቆመው እና ሊያፈርሰው አይችልም:: በቃን የሚያሰኝ ምንም ዓይነት ሁኔታ የለውም ፤ ይህንንም ለማፍረስ ባል ወይንም ሚስት ወይንም ሌላ ሶስተኛ ሰው ምንም ዓይነት ሥልጣን የላቸውም። የማንን ንብረት ማን ያበላሻል፤ ማንስ ይበትነዋል። እንዳንሳሳት የጋብቻው ባለቤት እግዚአብሔር እንደሆነ አንርሳ።

ጋብቻ ሲጀመርም በሞቅታ አይጀመርም፤ ሞቅታ የመቀዝቀዝ ባሕርይ አለው:: የሞቀ ይቀዘቅዛል አይቀሬ ነው። በማስተዋል፤ አርቆ በማሰብ፤ በጸሎት እግዚአብሔርን በመጠየቅ የሚጀመር ግን የመሞቅም የመቀዝቀዝም ባሕርይ የለውም፤ የራሱ የሆነ ዳር የሚያደርስ መርህ ያለው፤ ውስጡ ሕይወት ያለው ከምንም ነገር ጋር ያልተያያዘ፤ ብቻውን የሚገሰግስ፤ የተባለበት ቦታ የሚደርስ፤ ሞት ብቻ የሚያሸንፈው፤ የሚለየው፤ የሚያፋታው ውህደት ነው::

የዚህ ውህደት መነሻ ደግሞ ኪዳን ነው ፤ በንግግር፤ በጽሁፍ ሊገለጥ የሚችል ኪዳን። ኪዳን ማለት ያልነውን ወይንም የተናገርነውን አለማጠፍ፤ በተናገሩት ጸንቶ መቆም ማለት ነው። ይህም በእግዚአብሔርና በሰዎች ፤ በሰዎችና በሰዎች መካከል የሚፈጸም ነው። ኪዳን ሌላ ሁለተኛ ሰው ይፈልጋል።አንድ ሰው ብቻውን ፤ እራሱን በእራሱ በኪዳን ሊያስር አይችልም ። ቃልም ሊገባ አይችልም ። ምክንያቱም ኪዳኑ የሚሰጠው ሰው እስከ ሌለ ድረስ ፤ በኪዳኑ ተጠቃሚ የሚሆን እስከ ሌለ ድረስ ኪዳን የሚለው ቃል ትርጉም ያጣ ይሆናል።

መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚነግረን የመጀመሪያው ኪዳን የተጀመረው ደግሞ በኤደን ገነት ውስጥ መሆኑን ያሳየናል። የዚህ ኪዳን መነሻም የሰማይና የምድር የፍጥረት ሁሉ ፈጣሪ የሆነው አምላካችን እግዚአብሔር ነው።“ እግዚአብሔር አምላክም በአዳም ከባድ እንቅልፍን ጣለበት አንቀላፋም ከጎኑም አንዲት አጥንትን ወስዶ ሥፍራውን በሥጋ ዘጋው። እግዚአብሔር አምላክም ከአዳም የወሰዳትን አጥንት ሴት አድርጎ ሠራት ወደ አዳምም አመጣት ።” ዘፍ ምዕ 2፡21-22 ብሎ የሚነግረን፤ አዳም እግዚአብሔር ወደ እርሱ ያመጣትን ሴት ወደ እርሱ ካስጠጋ በኃላ እንዲህ ብሎ የኪዳን ቃል ተናገረ። “ ይህቺ አጥንት ከአጥንቴ ናት ሥጋም ከሥጋዬ ናት.......” ዘፍ ምዕ 2፡23፤ ከዚህ ኪዳን በኋላ “ ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል በሚስቱም ይጣበቃል ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ።” ዘፍ 2፡24 የሚለን፤ ይህ የእግዚአብሔር ቃል የኪዳኑ የመጨረሻ ማረጋገጫ ማህተም ሆነ ማለት ነው።

እንግዲህ ኪዳን መነሻ አለው፤ ኪዳን ፈጻሚ አለው ፤ ኪዳን ማሰሪያ አለው ። እንዳይነቃነቅ፤ እንዳይፈታና እንዳይፈርስ የሚያደርገው ጥልቅ በሆነ በአንድ ሥጋነት የተረጋገጠ፤ ታላቅ መንፈሳዊ ጥልቀት ባለው የእግዚአብሔር ቃል የታሰረ ነው። መጽሐፍ ቅዱሳችንን ስናጠና እግዚአብሔር ለህዝቡ ያለውን ቃል ኪዳን በብሉይም በአዲስ ኪዳንም ሲፈጽም እናያለን እኛም ጋ ሲደርስ እንዲሁ ነው።

ዛሬም ጋብቻችንን ስናስብ ዘወር ብለን ልናየው የሚገባው ዋናውና መሰረታዊ የሆነውን በእግዚአብሔርና በሰው ፊት የገባነውን ቃል ኪዳን ማስታወስ ነው:: በእርግጠኝነት ለመናገር የዚህ የቃል ኪዳን ልውውጥ ሥርዓት በሚኪያሄድበት ቀን ማናችንም ብንሆን ለተናገርነው የኪዳን ቃል ምንም ዓይነት ጥርጥር እንደሌለንና አንዳንዶቻችንም ከንግግር ባለፈ በእንባችን ጭምር ኪዳናችንን የገለጽንና ያረጋገጥን እንኖራለን። ስለዚህ ይህንን የገባነውን ኪዳን በማስታወስና በመጠበቅ እስከ ፍጻሜው ድረስ ልንጓዝ ያስፈልጋል፤

ከላይ እንደተጠቀሰው ኪዳን መነሻ እንዳለው፤ ፈጻሚ እንዳለው ፤ ማሰሪያ እንዳለው ሁሉ ኪዳን ማብቂያም አለው። በዚህ የማስታወሻ ጽሁፍ መሰረት የኪዳን ማብቂያው ሞት ብቻ ነው፤ ይህም ማለት እግዚአብሔር ወደ እኛ ያመጣትን ወይንም ያመጣውን እንደገናም በቃሉ ማህተም ካጸናው ሰው ጋር የምንለየው በሞት ብቻ መሆኑን አጥብቀን ልንረዳ ይገባል

ለዚህም ነው የእግዚአብሔር ቃል “ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል ከሚስቱም ጋር ይተባበራል ሁለቱም አንድ ስጋ ይሆናሉ የሚለውን ቃል አላነበባችሁም? ስለዚህ አንድ ሥጋ ናቸው እንጂ ወደ ፊት ሁለት አይደሉም፡፡ እግዚአብሔር ያጣመረውን እንግዲህ ሰው አይለየው፡፡” ማቴ 19፡5-6 በማለት በአንክሮ የሚመክረን። ይህ ቃል እግዚአብሔር ፈጥሮኛል ለሚል፤ ጋብቻዬን የሰራ እግዚአብሔር ነው ብሎ ለሚያምን ሁሉ የተደነገገ ሥርዓት ነው፤ የጋብቻው ባለቤት ያወጣው፤ የተናገረው የጋብቻ ሕይወት ቃል ነው። ሌላ መሰረት የምናደርገው ወይንም መነሻ የምናደርገው ምንም ዓይነት መመሪያም ሕግም የለንም። በመሆኑም ይህንን ቃል ይዘን ጋብቻችንን ዳር ማድረስ ይኖርብናል።

የምናምነው ነገር በኑሮአችን ላይ የበላይ እንደሚሆን ልንዘነጋ አይገባንም፤ በምናምነው ነገር ዙሪያ ሁሌ ስለምንመላለስና ስለምናስበው ልባችንና ፈቃዳችን ላመንበት ነገር የተገዛ ይሆናል። ነገራችንም ሁሉ የሚፈረጀው ከዛው በመነሳት ይሆናል፤ በእርሱ እይታ ይሆናል፤ በእርሱ እውቀት ይሆናል፤ በእርሱ ፍላጎት ይሆናል፤ በእርሱ ፈቃድ ይሆናል፡፡ ያመንንበት ነገር በሕይወታችን ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ የማድረግ ኃይል አለው።

ጉዳያችንን ወይንም ሁኔታችንን ለመረዳት ወይንም ለመፍታት ብንፈልግ መጀመሪያ እኛ ያለንበት ሁኔታ ወይንም ቦታ ወይ ሀገር በቅጡ ተለይቶ መታወቅ አለበት፡፡ ጉዳዮቻችን ሁሉ ሊፈቱ የሚችሉት ከምንኖርበት አካባቢ ወይንም ሀገር ደንብና ህግ ፤ ሥርዓት በመነሳት ነው እንጂ በዘፈቀደ የአንዱ ሀገር ደንብ ተነስቶ ባልኖርንበት፤ በማያውቁንና በማናውቃቸው ሕዝብ መካከል የሚሰራውን ህግ አንስቶ በእኛ ላይ ሊፈርድና ሊያስፈርድ ወይ ሊበይን አይችልም ፡፡ ቢፈረድብን በሀገራችን፤ ቢፈረድልን በሀገራችን፤ ቢያምርብን በሀገራችን፤ ብንከፋ በሀገራችን፤ ስለዚህ በዚህ ደንብ መሰረት እንከሰሳለን ደግሞም እንሾማለን።

ስለዚህ የእኛ የመኖርያ አድራሻ የት ነው? ሀገራችን የት ነው? የሀገራችንስ መመሪያና ህግ ምን ይላል ? እንግዲህ በእግዚአብሔር ዓምሳያ ተፈጥረናል ፤ የጋብቻዬ የትዳሬ ባለቤት እግዚአብሔር ነው የምንል ሁሉ ጉዳዮቻችንን ነገሮቻችንን የምንፈታው ጋብቻውን በፈጠረው ባለቤት መመሪያና ህግ መሰረት ነው። እውነቱማ በምድር እንኑር እንጂ ምድራዊዎች አይደለንም፤ ሥጋን የለበስን እንሁን እንጂ የሥጋና የፈቃዳችን ተገዥዎች አይደለንም። ሀገራችን በላይ በሰማይ ከክረስቶስ ጋር ነው፡፡ የእግዚአብሔር ቃል "እኛ አገራችን በሰማይ ነውና ከዚያም ደግሞ የሚመጣ መድኃኒትን እርሱንም ጌታን ኢየሱስ ክርስቶስን እንጠባበቃለን " ፊልፕስዩስ ምዕ.3:20

አገሩ በሰማይ የሆነ ደግሞ የአገሩ መንግስት የሚገዛበትን የሚያስተዳድርበትን ህግና ደንቡን፤ ሥርዓቱን ያውቀዋል። እኛም በእኛችን አለ ደግሞም እናውቀዋለን ። ይህ የእግዚአብሔር መንግሥት ደንብና ሥርዓት የተገለጸበት ታላቁ መጽሐፍ መጹሐፍ ቅዱስ ሲሆን ብቸኛ የህይወት መፍቻ ቁልፍ ነው:: አካሄድን፤ አኗኗርን የሚገልጽ፤ የሚያሳይ የሚመራ የህይወት ቃል ነው። በምድር ስንኖር እንደ ሰማያዊው መንግስት ልማድና ወግ ልንመላለስ ይገባል። ዛሬ ጋብቻችንን ትዳራችንን የምናይበት የምንመራበት በዚህ የእውነት ቃል ላይ ተመስርተን፤ የሚለንንም በማድረግ ብቻ ነው። " ትዕዛዙንም ብንጠብቅ በዚህ እንዳወቅነው እናውቃለን። አውቄዋለሁ የሚል ትእዛዙንም የማይጠብቅ ውሸተኛ ነው እውነትም በእርሱ ውስጥ የለም። ቃሉን ግን የሚጠብቅ ሁሉ በእርሱ የእግዚአብሔር ፍቅር በእውነት ተፈጽሟል። በእርሱ እንዳለን እናውቃለን።" 1ኛ ዮሐንስ 2:3-5

ቃሉን መጠበቅ፡- እናንተ ባሎች ሆይ

ሰው ለሚስቱ ያለውን ፍቅር ለመግለፅ የማያደርገው ነገር የለም። በብዙ ጌጦች በመሸለም፥ የፍቅር መግለጫ አበባዎች በማበርከት፥ እንደሚወዳት በቃሉ በመናገር፥ የተለያዩ ስጦታዎችን በመስጠት፥ በቤት ውስጥ በስራ በመርዳት፥ የቤት ውስጥ ፅዳት፥ ማብሰል፥ ልጆችን በመጠበቅ፥ ትምህርት ቤት በመውሰድ፥ ልብስ በማጠብ ወዘተ... በእነዚህ ሁሉ ሚስቱን ለማስደሰት የማይጥር የለም። ይህ አካሄድ ጠቃሚና እርስ በርስ ያለውን ግንኙነትና ፍቅርን ሊገልፅ የሚችል ቢሆንም ይህ ግንኙነት በሰው እና በሰው መካከል ስለሆነ አንዱ አንዱን አስደስቶ አይጨርስም። ወይንም እንደስራ ክፍፍል (ድርሻ) ይታይና ፍቅርን ቀስ ብሎ ከመሀል ሊያስወጣው ይችላል። በአንፃሩም ድርሽ የማይል፥ ሚስት ለስራ አገልግሎት የተፈጠረች አድርጎና እራሱን ከፍ አድርጎ የቀረበለትን ብቻ እየተመገበ የሚኖር አለ። በእርግጥ ስራው ሊሰራ ይችላል ግን ፍቅር ላይኖር ይችላል። ፍቅር ያበቃና መልኩ ተቀይሮ መረዳዳት ይሆናል። መረዳዳት ደግሞ ከርህራሄ የተነሳ ያሚመጣ እንጂ ፍቅርን ብቻ መሰረት ያደረገ ሊሆን ነው ለማለት አያስደፍርም። ርህራሄ ደግሞ ለሰው ካለን ሀዘኔታ የሚመነጭ ነው። ስለዚህ ትዳራችን ወንም ጋብቻችን የመረዳጃ ማህበር ወይንም ህብረት ሳይሆን በፍቅር ላይ የተመሰረተ መተሳሰብ ነው። ፍቅር ደግሞ 1ኛ ቆሮ. 13፡3-8 ላይ እንደተፃፈው "ድሆችንም ልመግብ ያለኝን ሁሉ ባካፍል፥ ስጋዬንም ለእሳት መቃጠል አሳልፌ ብሰጥ ፍቅር ግን ከሌለኝ ምንም አይጠቅመኝም። ፍቅር ይታገሳል፥ ቸርነትንም ያደርጋል፤ ፍቅር አይቀናም፤ ፍቅር አይመካም፥ አይታበይም፤ የማይገባውን አያደርግም፥ የራሱንም አይፈልግም፥ አይበሳጭም፥ በደልን አይቆጥርም፤ ከእውነት ጋር ደስ ይለዋል እንጂ ስለ

አመፃ ደስ አይለውም፤ ሁሉን ይታገሳል፥ ሁሉን ያምናል፥ ሁሉን ተስፋ ያደርጋል፥ በሁሉ ይፀናል። ፍቅር ለዘወትር አይወድቅም፤ ትንቢት ቢሆን ግን ይሻራል፤ ልሳኖች ቢሆኑ ይቀራሉ፤ እውቀትም ቢሆን ይሻራል።" ይህን ፍቅር በየትኛውም መንገድ በራሳችን ልናመጣው አንችልም። ይህን ፍቅር ለማግኘት ፍቅርን ያሳየንን ጌታችንን ልንመለከት ይገባል። እውነተኛውን ፍቅርም የምናገኘውም ከእርሱ ነው። ከዚህ በኋላ ነው ፍቅርን ልናስተላልፍ የምንችለው። በኤፌሶን መፅሀፍ ስለባልና ስለሚስት ግንኙነት ከመናገሩ በፊት የሚገልፀው "ለእያንዳንዳችሁ በክርስቶስ ፍርሀት የተገዛችሁ ሁኑ" ይላል። ይህ ማለት በክርስቶስ ውስጥ ያለውን ሀሳብና ፈቃድ ምን እንደሆነ ጠንቅቀን እንድናውቅ ይመክረናል። ስለዚህ የምናደርገው ሁሉ ስለክርስቶስ ብለን እንጂ ስለሚስት ወይም ስለባል ብለን አይደለም። ሰውን በቀጥታ ማስደሰት አይቻልም፤ ሰውን ለማስደሰት የምንችለው እኛ በክርስቶስ ሀሳብና ፈቃድ ውስጥ ስንጠቀለል ብቻ ነው። ምክንያቱም የመልካም ነገሮች ሁሉ ምንጭ ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ስለሆነ ነው።

ስለዚህ በእውነተኛው ፍቅር ላይ የተመሰረቱ የፍቅር መግለጫ ተግባራት የማንንም የፍቅር ምላሽ ሳይጠብቁ ማድረግ የሚገባቸውን ሁሉ እያደረጉ ፍቅርን ያጣጥሙታል፥ ያሳድጉታል፥ ይደሰቱበታል። የፍቅር ጌታ የሆነውን ያመሰግኑበታል። ለዚህ ነው ጳውሎስ በኤፌሶን 5፡23 ላይ "እናንተ ባሎች ሆይ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን እንደወደደ ሚስቶቻችሁን ውደዱ" ብሎ የተናገረው። የመረዳዳት ነው ብላችሁ ታስቡ ይሆን? አይመስለኝም። ዘርዘር አድርጎ ሲናገር የባልና የሚስት ግንኙነት በክርስቶስ እና በቤተ ክርስቲያን መካከል እንዳለው አይነት ግንኙነት አድርጎ ይናገራል። ምን ያህል የጠለቀ እንደሆነ ያሳየናል። ክርስቶስ በቃሉ ሀይል ቤተ ክርስቲያንን እንዲቀድሳት፥ እንዲያጥባት፥ እንዲያነፃት ብሎም እራሱን አሳልፎ እንደሰጠ ሁሉ ባሎችም እንዲሁ እንድናደርግ ያስታውቀናል። ከዚህ ውስጥ የወጣ ፍቅር አበባ ቢሰጥ ያምርበታል፥ በየእለቱ መውደዱን ቢገልፅ ያምርበታል፥ በቤት ውስጥ ሚስቱን ቢረዳ፥ ቢያግዝ እውነት አለው፥ ያለምክንያት ሁሉን ያደርጋል፥ ምንም አይነት ምላሽ ከሚስቱ አይጠብቅም፤ እንዲያውም ከላይ ከተጠቀሱት በላይ ለመሰዋት የተዘጋጀ ይሆናል እንጂ ከሚስቱ የጣፈጠ ምግብ ወይንም ሚስቱ ከምታደርግለት ተነስቶ ማፍቀሩን አይወስንም። የሚወድድበት መሰረት አለው - ክርስቶስ ቤተክርስቲያንን በብላሽ፥ በነፃ እንደወደደ ማለት ነው። ፍቅርን ለመማር ወደ ኢየሱስ፤ ከኢየሱስ ያገኘነውን እውነተኛ ፍቅር እግዚአብሔር አካል አድርጎ ለሰጠን ለሚስት መግለፅ፥ በተግባር ማሳየት።

ቃሉን መጠበቅ፡- እናንተ ሚስቶች ሆይ

ባሎቻቸውን በመንከባከብ፥ ቤታቸውን በማፅዳት፥ ውበታቸውን በመጠበቅ፥ በቤት ውስጥ ያለውን ሁሉ ጉልበታቸውን ሳይቆጥቡ የሚሰሩ ለባሎቻቸው የተመረጠውን በማቅረብ ለባሎቻቸው ያላቸውን ፍቅር በተለያየ መንገድ የሚገልፁ በባሎቻቸው የሚኮሩ፥ እንደዋርካ ጥላ ባሎቻቸውን የሚያዩ፥ ከራሳቸው ይልቅ የባሎቻቸውን ደስታ በማየት የሚደሰቱ፥ የሚፈነድቁ ቢኖሩም ደግሞ ባሎቻቸውን ዝቅ አድርጎ የማየት እና ብሎም የበላይነት መንፈስ ያላቸው ይኖራሉ። እነዚህ ሁለት መንገዶች የየራሳቸው በውስጥ የሚኖር መነሻ ሀሳብ አላቸው። ባልን ለማስደሰት ተብሎ የሚደረገው ነገር ሁሉ መልካም ቢሆንም በድርጊት ላይ ብቻ የተመሰረተ፥ መነሻ የሌለው ስለሆነ ዘላቂነት አይኖረውም፤ በተጨማሪም አስደስቶ መጨረስ አይቻልም። እንደዚሁም የበላይ ሆኖ ቤትን ለማስተዳደርና በባል ላይ መሰልጠን ደግሞ የትም የማያደርስ ከመሆኑም በላይ ትዳሩን ሆን ብሎ ለመበተን የተሰራ ልዩ የሆነ ሰይጣናዊ ስሜት ነው። እነዚህ የጠቀስናቸው ሀሳቦች ሁሉ በቀጥታ ከሰው ጋር የተገናኙ ስለሆኑ ስኬት አልባ፥ ውጤተ ቢስ ይሆናሉ። ከግል ፍላጎት ተነስቶ የሚደረጉ ስለሆነ በባል ፊት ሞገስ ለማግኘት ከተፈለገ ብቸኛው አማራጭ ባልን አይቶ የሚፈልገውን እየፈላለጉ በማድረግ ሳይሆን ክርስቶስን በማየት የሚገኝ ድርጊት ዘለቄታዊ የሆነ የሰመረ ግንኙነትን በባልና በሚስት መካከል ይፈጥራል።

ጋብቻችንን የሰራው እግዚአብሔር ነው ብለን የምናምን ሁሉ ይህን ጋብቻ እንዴት አድርገን እንደምንመራውም መማሪያ ሰጥቶናል፤ ማድረግ የሚገባንንም ነግሮናል። በዘፈቀደ ወይንም ባወጣው ያውጣው ተብሎ አይመራም፥ አይኬድም። ስለዚህ መፅሀፍ ቅዱስ ለሚስቶች የተፃፈውን በህይወታችን ልንተረጉመው ይገባል።

"ዳሩ ግን ቤተ ክርስቲያን ለክርስቶስ እንደምትገዛ እንዲሁ ሚስቶች ደግሞ በሁሉ ለባሎቻቸው ይገዙ።" - ኤፌ 5፡24

"ሚስቶች ሆይ፥ ለጌታ እንደምትገዙ ለባሎቻችሁ ተገዙ" - ኤፌ 5፡22

"ክርስቶስ ደግሞ የቤተ ክርስቲያን ራስ እንደ ሆነ እርሱም አካሉን የሚያድን እንደ ሆነ ባል የሚስት ራስ ነውና" ኤፌ 5፡23

ብዙዎቻችን መገዛት የሚለው ቃል ያስደነግጠናል። ምናልባትም በአንድ ፈላጭ ቆራጭ ስር የወደቅን፥ ምንም መብት የሌለን አድርገን ልንቆጥረው እንችላለን። በዚህ የእግዚአብሔር ትእዛዝ ላይ የሚነገረን መገዛት ግን በቤተክርስቲያን እና በክርስቶስ

መካከል ያለውን ግንኙነት ለማሳየት ነው። "ቤተክርስቲያን ለክርስቶስ እንደምትገዛ" ይህ የመገዛት ትልቁ ሀሳብ ያለበት ክፍል ነው። ደግሞም እንደክርስቲያን ስናነበው ብዙም ውስብስብ አይሆንብንም ምክንያቱም ቤተክርስቲያን ፈቃዷን ለክርስቶስ በመስጠት ክርስቶስ በእሷ ላይ መሪ እንዲሆን ወድዳ እራሷን እንደሰጠች እንጂ ተገድዳ በእርሱ ስር እንድትወድቅ አይደለም። እኛም ፈቃዳችንን ለክርስቶስ ስለሰጠን እርሱ ጌታችን መድሀኒታችን መሪያችን እንዲሆን እንዳደረግን ሁሉ ዛሬም ሚስቶች በፈቃዳቸው ራሳቸውን ለባሎቻቸው እንዲሰጡ ይህ ክፍል ያሳስበናል። ክርስቶስ የቤተክርስቲያን ራስ እንደሆነና እንዲሁም ባሎች የሚስት ራስ እንደሆኑ በተከታዩ ክፍል ላይ ይገልፃል። ይህ ለባሎች የተሰጣቸው ስፍራ ሲሆን ሚስት የባል ራስ ትሁን ቢባል በክርስቶስ እና በቤተክርስቲያን መካከል ያለውን ህብረት እና አንድነት እንደመገልበጥ ያህል ነው። ምንም እንኳን ይህ ቃል በዚህ ሁኔታ ቢያስተምረንም ሰው በገዛ ፈቃዱ ይህንን ሊያደርግ ይቸገር ይሆናል። ሆኖም ግን መጀመሪያ ላይ እንደተናገረው በኤፌሶን 5፡20 ላይ "ለእያንዳንዳችሁ በክርስቶስ ፍርሀት የተገዛችሁ ሁኑ" ስለሚል በክርስቶስ ውስጥ በሚገኝ ፍርሀት፥ ክርስቶስን በመመልከት፥ እሱን በማየት እራስን የመስጠት መረዳት ከእዛ ይገኛል። ስለዚህ ሚስቶች ለክርስቶስ ያላቸው መረዳት እራሳቸውን ለባሎቻቸው ለመስጠት አይቸግራቸውም - እንደ ቤተክርስቲያን።

ይህንን መሰረት በማድረግ ለባሎቻችን የምናደርጋቸው እንክብካቤዎች ሁሉ፥ ልናስደስታቸው የምንጥርባቸው መንገዶች ሁሉ፥ ለባሎቻችን ፍቅራችንን የምንተረጉምባቸው በመጀመሪያ ላይ የገለፅናቸው አካሄዶች ሁሉ መነሻ ያላቸው በመሆኑ ከባሎች ምላሽ እንኳን ባይገኝ የሚገባቸውን እያደረጉ በእግዚአብሔር እና በሰው ፊት የገቡትን ቃል ዳር ለማድረስ ፈፅሞ አይቸገሩም። ምክንያቱም ቃሉን ለማድረግ የተፃፈውን ለመፈፀም እራሳቸውን ለክርስቶስ ሰጥተዋልና። ስለዚህ ግንኙነቱ በቀጥታ ከባል ጋር ሳይሆን ከክርስቶስ ጋር ይሆናል። ከዚህ የተነሳ ደግሞ ከክርስቶስ የሚመጣው ሰላም ለቤቱ ሁሉ ሰላም ይሆናል። አንዳንድ ባሎች በዚህ ክርስቶስ ለሰጣቸው ክብር እራሳቸውን ባለመስጠት በሚስቶቻቸው ላይ የክርስቶስን ሳይሆን በውስጣቸው ያለውን የራሳቸውን የስጋ ፈቃድ እና ትምክህት የሚያደርጉ እንኳን ቢኖሩ ሚስቶች አሻፈረኝ እንዳይሉ የእግዚአብሔር ቃል ተሰጥቶአቸዋል። "እንዲሁም፥ እናንተ ሚስቶች ሆይ፥ ከባሎቻችሁ አንዳንዱ ለትምህርት የማይታዘዙ ቢኖሩ፥ በፍርሀት ያለውን ንፁሁን ኑሮአችሁን እየተመለከቱ ያለ ትምህርት በሚስቶቻቸው ኑሮ እንዲገኙ ተገዙላቸው።" 1ጴጥ 3፡1-2። ጴጥሮስ ይህንን ቃል ስላልዳኑ ባሎች እንኳን የፃፈ ቢሆን ድነውም ካልዳነው ሰው ህይወት እንኳን ያልተሻለ ህይወት የሚኖሩ ባሎች እንዳሉም መገንዘብ ያስፈልጋል።

እንግዲህ የእግዚአብሔር ቤተ ሰዎች ሆይ በዚህ አለም ውስጥ የምንኖር ብንሆንም የእኛ ጉዳይ እና ነገራችን የሚፈታው እና የሚታየው በሰማያዊው መንግስት ወግና ስርአት ስለሆነ ይልቁንም ጋብቻችንን ለመጠበቅ ወደ ህጉ እና ደንቡ ዘወር ልንልና ልናስተውል ይገባል። ቃሉን በመጠበቅ ውስጥ የሚጓዝ ጋብቻ ወይም ትዳር ያለሀሳብ እግዚአብሔር እስካለበት ቀን ድረስ መጓዝ ይችላል። ይህ ማለት አልጋ በአልጋ ይሆናል ማለት ሳይሆን በችግርና በመከራም ጊዜ መፍትሄውን በቃሉ ውስጥ ማግኘት ስለሚቻል ነው። ችግሮቻችንን የምንፈታባቸው ቁልፎች በበዙ ቁጥር ችግሮቻችን እየጨመሩና እየበዙ ይሄዳሉ እንጂ ማብቂያ አይኖራቸውም። አንድ ቁልፍ አለ ይኸውም ህያው የእግዚአብሔር ቃል ብቻ።

ይህንን ቃል በመታዘዝ፤ በህይወት በመተርጎም፤ ለባላችንና ለሚስታችን ከመነሻው በእግዚአብሔርና በህዝቡ ፊት የገባነውን ኪዳን በማስታወስ ኪዳኑንም በመጠበቅ የኪዳኑ ፈፃሚ መሆናችንን ሳንዘነጋ እለት እለት በማሰላሰልና በመፀለይ ጋብቻችንን ህይወት እየሰጠነው የኪዳኑ ማብቂያ ጊዜ የተቆረጠችው የመጨረሻዋ ቀን ድረስ ፀንተን ልንቆም ያስፈልጋል። ኪዳኑን ያፀናልን የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር የሚያስችለውን ጸጋ ሊሰጠን የታመነ ስለሆነ አይኖቻችንን ወደ እርሱ ብቻ እናንሳ።

የእግዚአብሔር ጸጋና ሰላም ከሁላችን ጋር ይሁን። ጋብቻችንም የተባረከ ይሁን አሜን።